

Christian College • Not to be reproduced.

ህጉን ካነበቡ በኋላ የእስራኤል ህዝቦች ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን ለማድረግ ወሰኑ። ለእርሱ ታማኝ ለመሆን ወሰኑ። ለእርሱም ታማኝ ለመሆን ቃል ገቡ።

ይህ ቃል ኪዳንና በኪዳኑ ሰነድ ላይ ፊርማቸውን ያሰፈሩት ስም ዝርዝር በነህ 10 ላይ ተጽፎአል።

ይህ ኪዳን እግዚአብሔር ከሰብአዊ ዘር ጋር ባደረገው ዘላለማዊ ኪዳን ውስጥ ተካቷል።





- ዘላለማዊ ኪዳን:
  - ኪዳን ለምን አስፈለገ?
  - ኪዳን ወይስ ኪዳናት?
  - ኪዳናዊ አወቃቀር
- የእስራኤል ኪዳን (ነህ 10):
  - ለመታዘዝ ቃል መግባት
  - ለማምለክ ቃል መግባት

ኪዳን ለምን አስፈለገ?

“የቀሩት ሕዝብ፦ ... በሙሴ አማካይነት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ሕግ የጌታችንን የእግዚአብሔርን ትእዛዞች፣ ደንቦችና ሥርዐቶች ሁሉ ለመታዘዝ በዚህ ርግማንና መሐላ ቃል ገቡ።” *(ነህ 10:28-29)*

ህዝቡ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር በሲና ተራራየገባውን ኪዳን ለመፈጸም ቃል ገቡ። (ዘጸ 19:8; 24:3 ይመ)።





ስዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በሃጢአት ውስጥ ሲወድቁ እግዚአብሔር ኪዳን አዘጋጀ። (ዘፍ 3:15)።

ሃጢአት እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር የነበረውን ግንኙነት አበላሸ። እግዚአብሔር ግን ይህንን የተበላሸ ግንኙነት ለማደስ ቆርጦ ተነሳ።



እያንዳንዱ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን ለማድረግና ህብረታቸውን ለማደስ አልያም ለመቃወም መምረጥ ይችላል።



ኪዳን ለምን አስፈለገ?

- የተከፋፈለ ሰብአዊ ዘር
  - ቃየን
    - ክፋትን መረጠ
      - ላሜክ(7ኛ ትውልድ)
        - ብዙ ሚስቶችን ማግባት አስተዋወቀ
          - በውሃ ጥፋት ተወገዱ
  - ሴት
    - እግዚአብሔርን ተቀበለ
      - ሔኖክ (7ኛ ትውልድ)
        - ከእግዚኤብሔር ጋር ተራመደ
          - ኖህ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አገኘ።

እንደ እኛ ሃጢአት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት የማደስ ስራው ላይ ተስፋ አልቆረጠም። ዘላለማዊ ኪዳኑን ብዙ ጊዜ ሲያድስልን እናያለን።





ኪዳን ወይስ ኪዳናት?

“ጆሮአችሁን ከፍታችሁ ወደ እኔ ቅረቡ፤ነፍሳችሁም እንድትኖር አድምጡኝ።ለዳዊት በገባሁት በጽኑ ፍቅሬ፣ከእናንተም ጋር የዘላለም ኪዳን አደርጋለሁ።” *(ኢሳ 55:3)*

ከውሃ ጥፋት በኋላ፣ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ኪዳን አደረገ፣ ከይስሐቅና ከያእቆብ ጋርም ያንኑ ኪዳን አጸና። (ዘፍ 17:1-8, 19; 1 ዜና 16:16-17; ገላ 3:17).



በሲና ተራራ፣ እግዚአብሔር ከእስራኤል ልጆች ጋር ኪዳን አደረገ (ዘጸ 19-24). ይህ “አሮጌው ኪዳን” (2 ቆሮ 3:14) የዳዊትን ቤት ጭምር የሚጠቅስ ነው (ኢሳ 55:3).



በመጨረሻም እግዚአብሔር “አዲስ ኪዳን” ከህዝቡ ጋር ለማድረግ ቃል ገባ (ኤር 31:33-34). ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ሁሉ ኪዳናት የአንዱ የዘላለማዊው ኪዳን የተለያዩ ገጽታዎች ናቸው። ዘላለማዊው ኪዳን የሚከተሉትን ያካትታል:-

1. ቅድስናን (ኤር 31:33)
2. እርቅን(ኤር 31:33)
3. ተልእኮን (ኤር 31:34)
4. ጽድቅን (ኤር 31:34)




ኪዳናዊ አወቃቀር

“እግዚአብሔር ይህን ቃል ኪዳን የገባውም ከአባቶቻችን ጋር ሳይሆን፣ ዛሬ እዚህ በሕይወት ከምንገኘው ከእኛ ከሁላችን ጋር ነው።” (ዘዳ 5:3)



በዚያን ጊዜ የሚደረጉ ኪዳኖች የተለያዩ ክፍሎች ነበሯቸው። የዘዳግም መጽሐፍ(የኪዳን መጸሐፍ) በመባል የሚታውቅ ሲሆን) እንደዚሁም ኢያሱ ከህዝቡ ጋር ያደረገው ኪዳናት ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናቸው።



መግቢያ	
ዘዳ. 1:1-5	ኢያሱ. 24:2
ታሪካዊ ማብራሪያ	
ዘዳ. 1:6-4 – 4:43	ኢያሱ. 24:2-13
የሕግ ዐጭር ቃኘ	
ዘዳ. 4:44 – 26:19	ኢያ. 24:14-15, 23
በረከቶችና መርገሞች	
ዘዳ. 27-30	ኢያ. 24:19-20
ምስክሮች	
ዘዳ. 30:19	ኢያ. 24:22, 27
ልዩ መመሪያና ጥቅም	
ዘዳ. 31:9-13	ኢያ. 24:25-26

“ምንም እንኳን ይህ ኪዳን በመጀመሪያ ከአዳም ጋር የተደረገና በኋላም ከአብርሃም ጋር የታደሰ ቢሆንም፣ ክርስቶስ እስኪሞት ድረስ ሙሉ በሙሉ የጸና አልነበረም። የመጀመሪያው የድነት ፍንጭ ከተሰጠበት ጅምሮ ይህ ኪዳን በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ የተመሰረተ ነበር። ሰዎችም ይቀበሉት ነበረው በእምነት ነበር። ነገር ግን በክርስቶስ ሞት ሲጸና፣ አዲስ ኪዳን ተብሎ ተጠራ። የእግዚአብሔር ህግ የዚህ ኪዳን መሰረት ነው። ይህ ኪዳን ሰዎችን እንደገና ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ፈቃድ ጋር የተስማሙ እንዲሆኑና እግዚአብሔርን ሊታዘዙ ወደሚችሉበት ስፍራ ለማምጣት የሚያዘጋጅ ነው። ”

E.G.W. (Patriarchs and Prophets, cp. 32, p. 370)


ለመታዘዝ ቃል መግባት

“ያተሙትም እነዚህ ናቸው፤የሐካልያ ልጅ አገረ ገዡ ነህምያ፣ሴዴቅያስ፣ [እና 82 ተጨማሪ ሰዎች].” (ነህ 10:1)

84ቱ ፊራሚዎች ህዝበ እስራኤልን ወክለው ነበር። ገዢው በመጀመሪያ ፊረመ፤ ከዚያም ሊቀ ካህናቱና፣ ካህናቱ፣ ሌዋዊያና የህዝቡ መሪዎች ተከትሉ። ሁሉም የእግዚአብሔርን ህግ ለመታዘዝ ቃል ገቡ (ቁ. 29)።



የሚከተሉትን ነጥቦች አትኩረውባቸው ነበር።



እስራኤላዊያን ያልሆኑትን ላለማግባት (ቁ. 30)



ሰንበትን ለመጠበቅ(ቁ. 31)



የሰንበትን አመት በማክበር እዳዎችን በመሰረዝ ለድሆች ጥንቃቄን ለማድረግ(ቁ. 31)



የቤተመቅደሱን አገልግሎቶች ለመደገፍ(ቁ. 32-39)

እነዚህን መመሪያዎች መከተልና መልካም ልማዶችን መለማመድ ወደ ቅድስና ለማደግ የሚያስችሉ ናቸው።

ለማምለክ ቃል መግባት

“እኛም የአምላካችንን ቤት ቸል አንልም።” *(ነህ 10:39)*

ቤተመቅደሱን በተመለከተ ምን ለማድረግ ነበር ቃል የገቡት?




ለእለታዊው መስዋእት፣ ለበአላትና ለቤተመቅደሱ ወጪዎች ድጋፍ መስጠት

ለሌዋዊያን አስራት ለመስጠት፣ ሌዋዊያን ከተቀበሉት አስራት አስራት ይሰጡ ነበር

በመሰዊያው ላይ እንጨት እንዲቀጣጠል ማድረግ



የእርሻቸውንና የከብቶቻቸውን በኩራት ለመስጠት





ዛሬ በኢየሩሳሌም የቀድሞው ቤተመቅደስ የለም። ኢየሱስ በደሙ አዲሱን ኪዳን ሲፈርም፣ እነዚህ ጊዜያዊ ትእዛዛት ተሽረዋል።

ነገር ግን፣ ሰማያዊ ቤተመቅደስ አሁንም ቢሆን የዘላለሙ ኪዳን የደህንነት እቅድ የሚከናወንበት ማእከል ነው። (እብራውያን 8:1-7)

E.G.W. (The Ministry of Healing, cp. 11, p. 176)

“እግዚአብሔር የምርጫ ነጻነት ሰጥቶናል። ያንን መጠቀም የእኛ ድርሻ ነው። ልባችንን መቀየር አንችልም፤ ሃሳባችንንምና ስሜቶቻችንን መቆጣጠር አንችልም። ራሳችንን ንጹህ ማድረግ፣ እንደዚሁም ለእግዚአብሔር አገልግሎት ማብቃት አንችልም። ነገር ግን እግዚአብሔርን ለማገልገል መምረጥ እንችላለን። ፈቃዳችንን ልንሰጠው እንችላለን። ከዚያም እርሱ እንደ በጎ ፈቃዱ በእኛ ውስጥ መፈለግንም ማድረግንም ይሰራል። በዚህም መልኩ ሁለንተናችን በክርስቶስ ቁጥጥር ስር ይሆናል። ”

“በመሥዋዕት ከእኔ
ጋር ኪዳን
የገቡትን፤ቅዱሳኔን
ወደ እኔ
ሰብስቧቸው ::”

መዝ 50:5